# ዲያስፖራዎች “መደመራችንን” በምን መልክ እናሳይ?

አክሎግ ቢራራ (ዶር)

“እኛ እትዮጵያዊያን ስንኖርም፤ ስንሞትም ኢትዮጵያዊ ነን”

ጠ/ሚንስትር ዶር ዐብይ አሕመድ

ባለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ትኩረታችን ህወሓት መራሹ ኢህአዴግ በፈጸመው ኢ-ሠብአዊነቱና ጸረ-ፍትሃዊነቱ፤ በሚዘገንነው በጸረ-ኢትዮጵያና ጸረ-ኢትዮጵያዊነቱ፤ በአፈኝነቱና በጨካኝነቱ፤ በጸረ-ሕዝብና በጸረ-ዲሞክራሲነቱ፤ በድርጅታዊ መዝባሪነቱና በሌብነቱ ወዘተ ዙሪያዎች ላይ ነበር። ባለፉት ሶስት ዓመታት በወጣቱ ትውልድ፤ በተለይ በቄሮውና በፋኖው መስዋእትነትና እምቢተኛነት የተመራው የሕዝብ ትግል፤ በተለይ “ወያኔ/ህወሓት” በቃ መፈክር ቀስቃሺነት እና በውጭ ባለው ተቆርቋሪ ኃይል ደጋፊነት ኢትዮጵያ አዲስ ተስፋ የሚሰጥ ምእራፍ ጀምራለች።

ይህ ሕዝባዊ እምቢተኛነት በማንም ኃይል ሊመለስ አይችልም። የዚህ ሕዝብ ፍላጎትና ምኞት ግለሰቦችን በሌሎች ግለሰቦች መተካት ሳይሆን፤ መሰረታዊ ለውጥ ተካሂዶ ለመጀመሪያ ጊዜ **<u>የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣኑ ባለቤትና የአገሩ የተፈጥሮ ኃብት ባለቤት</u>** እንዲሆን ነው። ኢትዮጵያ ሕዝብን የእድገቱ መዓከል ያደረገ፤ አገር ተከል ልማት ያስፈልጋታል የሚል ጽንሰ ሃሳብ በተደጋጋሚ የማቀርበውም ለዚህ ነው። ይህን ለማድረግ ገና ያልተዳሰሰ ኃይል አለ። የውጭ እዳውም ሸክም ሆኗል፤ መከፈል አለበት። **<u>“እትዮጵያ ሃገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ”</u>** እንዲሉ፤ እዳውን የተሸከመው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሆን ተጠቃሚዎቹ ግን የውጭ ምንዛሬውን ያባከኑትና ከአገር ያሸሹት ናቸው። ይህ እንዳለ ሆኖ፤ ችግሩን እንዴት እንፍታው የሚለውን አስቀድማለሁ።

ጠ/ሚንስትር ዶር ዐብይ የተመረጡት ከላይ በጠቀስኳቸው በወጣቶችና በአብዛኛው ሕዝብ ድጋፍ መሆኑን በተለያዩ ሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፎች አይተናል። እኒህ መሪ የሕዝብ አገልጋይ መሆናቸውን በተደጋጋሚ ገልጸዋል።

የዚህ አጭር ማስታወሻና ወገናዊ ጥሪ ምክንያት፤ **<u>“እኛስ”</u>** በውጭ የምንኖረው አገር ወዳዶች ለአገራችንና ለመላው ሕዝቧ ምን የሚታይና የሚዳሰስ አስተዋፆ ለማድረግ እንችላለን የሚለውን ወቅታዊ ጥያቄ ለመመለስ ነው።

ያልተፈቱ የፖሊሲ፤ የፕሮግራምና የመዋቅር ጥያቄዎች እንዳሉ ሆነው፤ ግን፤ ዛሬ ኢትዮጵያ የምትገኝበት የሶሲኦ-ኢኮኖሚክ ተግዳሮት እጅግ በጣም አሳሳቢ ከሆነ ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ይህ ሁኔታ አጥጋቢ በሆነ ደረጃ መፍትሄ ካላገኘ፤ ዛሬ አፍራሽና **ጠብአጫሪ** ወገኖች የሚያራቡትና የሚቀሰቅሱት “አመጽና ተቃዋሚነት” ሊስፋፉ ይችላል የሚል ስጋት አለኝ። ቢሆንም፤ የተነሣውን ሕዝባዊ አመጽ ሊያቆመው የሚችል ኃይል የለም ከሚሉት ወገኖች አንዱ ነኝ። በተጨማሪ፤ አሁን የተከሰተው የውጭ ምንዛሬ **<u>ቀውስ ቀስ በቀስ ሊፈታ ይችላል</u>** ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ።

**<u>“እኔስ ለሃገሬ”</u>** ምን ልሰራ እችላለሁ የሚለውን በፕሮጀክት መልክ ላቅርበውና አገራዊ ጥሪ ለዲያስፖራው ላድርግ።

1. ስድሳ በመቶ (60 %) የሚሆነውን ዘመናዊ ኢኮኖሚ በበላይነት የያዙት የፓርቲና የመንግሥት ተቋማት ናቸው፤ የግል ክፍሉ ጫጩት ነው። የግል ክፍሉ ከእስር ቤት ነጻ መውጣት አለበት፤

2. የአገርና የውጭ ብድር በገፍ የተበደሩት ከላይ የተጠቀሱት፤ በተለይ በአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ስር ያሉ የኢኮኖሚ ክፍሎች ናቸው፤ **<u>60 በመቶ የሚሆነውን</u>** የአገር ውስጥ ብድር (የተበደሩትን) ዲፎልት (ለመክፈል አንችልም) በሚል መልክ አቅርበው፤ የተበደሩትን እንኳን እንዳይከፍሉ የተደረጉት ህወሓት የሚቆጣጠራቸው እንደ ኤፎርት ያሉ ድርጅቶች ናቸው፤

3. በመንግሥት ስም የንግድ ብድር በውጭ ምንዛሬ መልክ የተበደሩት የመንግሥትና የፓርቲ ኩባንያዎች ናቸው፤ እዳውን የተሸከመችው አገሪቱ ናት፤

4. ተበዳሪዎቹ የአገር ውስጡንና የውጩን ብድር እንደ ግድብ፤ ሃዲድ፤ የስኳር ፋብሪካዎችና ሌሎች ግዙፍ ፕሮጀክቶችንና ዋጋ ቢስ የሆኑትን (White Elephant type mega projects) ለመሰረተ ልማት ውሏል እያሉ፤ ያመረቱት ውጤት ግን ለህዝብ አልቀረበም፤ የውጭ ምንዛሬ እንደባከነና እንደተሰረቀ በተደጋጋሚ በመረጃዎች ቀርበዋል፤

5. ለታላቁ የተሃድሶ ግድብ ፈሰስ የሆነውን፤ **<u>በግምቱ $5 ቢሊየን የደረሰውን</u>** ፈሰስ ያዋጡት ሕዝቡና መንግሥት ናቸው። የቻይናው State Grid of China Electric Power Equipment and Technology **<u>$1 ቢሊየን የንግድ ብድር ሰጥቶ</u>**

የኤሌክትሪኩን መስመር ዘርግቷል ወይም በመዘርጋት ላይ ነው። ይህ ብድር መከፈል አለበት። ግድቡ ያስተማረኝ ነገር፤ ኢትዮጵያዊያን ከተባበሩ ተአምር ለመስራት እንደሚችሉ ነው። አገር ተከል ኢኮኖሚ የሚመሰረተው ራስን በመቻል መሆኑን ያሳያል። የጎደለውን የውጭ ምንዛሬ፤ ውጭ የምንኖረው የማሟላት እድል አለን። ግድቡ ሲያልቅ፤ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ያስገኛል፤ ይህ ግድብ አይሰረቅም። የሁሉም ኢትዮጵይዊያን ኃብት ነው፤

6. የአዲስ አበባው ሃዲድ፤ ከአዲስ አበባ-ጂቡቲ የተዘረጋው 759 km ሃዲድ መንገድ የኢኮኖሚና የማህበረሰብ አገልግሎት ጥቅማቸው ከፍ ያለ ነው። የሁለተኛው የሃዲድ መንገድ ጠቅላላ ወጭ **<u>እስከ $4.5 ቢሊየን ደርሷል</u>** የሚል ግምት አለ፤ ከዚህ ፈሰስ **<u>$3 ቢሊየን</u>** ከቻይና Exim Bank የተገኘ የንግድ ብድር ነው። በጠቅላላው የኢትዮጵያ የሃዲድ ኮርፖሬሽን የውጭ እዳ **<u>$3.7 ቢሊየን (2016)</u>** ደርሷል። ይህ እዳ መከፈል አለበት፤

7. ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልከው የኤክስፖርት መጠን እየቀነሰ ሄዶ **<u>በ2015 $3.4 ቢሊየን የነበረው በ2017 ወደ $2.8</u>** ቢሊየን ወርዷል፤

8. ኢትዮጵያ ከውጭ የምትሸምተው መጠን **<u>በ2015 $15 ቢሊየን</u>** የነበረው በሁለት **ዓመታት በ2017 $17-$19 ቢሊየን ከፍ** ብሏል፤

9. ከ2014-2016 የኢትዮጵያ እዳ በአስር ነጥቦች ከፍ ብሏል፤ **<u>በ2015 $26 ቢሊየን የነበረው በ2017/2018 $29 ቢሊየን ደርሷል፤</u>** ከአገሪቱ **<u>ጠቅላላ ገቢ 56 በመቶ</u>** በላይ ይገመታል። ምርትና ኤክስፖርት እየጨመረ ቢሄድ ኖሮ ይህ ችግር በቀላሉ ይፈታል፤

10. ሆኖም፤ ኢንቬስትመንቱ አምራች ስላልሆነና ለዜጎች ህይወት መሻሻል ፋይዳቢስ ስለሆነ፤ የአገሪቱ የውጭ እዳ መጠን አሳሰቢ ደረጃ ላይ ደርሷል። የኢኮኖሚው መዋቅር ባለፉት ሃያ ሰባት አመታት አመርቂ ለውጥ አላሳየም። የኢንዱስትሪው ክፍል 22 በመቶ፤ የአገልግሎቱ 42 በመቶና የእርሻው ክፍል 34 በመቶ ናቸው። የገጠሩ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ትኩረት ያስፈልገዋል። ይህ ክፍል ዲያስፖራው ወደፊት ሊረባረብበት የሚያስችል እድል ይሰጠናል።

***ምን እናድርግ?***

***የአዲሱ ጠ/ሚንስትር መንግሥት የወረሰው ኢኮኖሚ፤ በተለይ የውጭ ምንዛሬ ተግዳሮት ስርዓት ወለድ ነው፤ መፈታት አለበት። ከአሁን በኋላ የውጭ ምንዛሬ የማይሰረቅበትና ከአገር የማይሸሸበት ሁኔታ ስለተፈጠረና በመመቻቸት ላይ ስለሆነ፤ እኛ በዲያስፖራው ዓለም የምንኖር ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ለአገራችንና ለመላው ህዝቧ ያለብንን ግዴታ ለመወጣት የሚያስችሉን እድሎች ተፈጥረዋል።***

***ጠ/ሚንስትሩ ለፓርላማው ንግግር ሲያደርጉ ዲያስፖራው በቀን አንድ ዶላር እንዲያዋጣ ጥሪ አድርገዋል። በውጭ የሚኖረው ዲያስፖራ እስከ አራት ሚሊየን ቢገመትም፤ ለማዋጣት የሚችለው ወይም አቅም ያለው መጠን አይታወቅም። ፈቃደኛነትና ቁርጠኛነት ካለ ግን፤ <u>በቀን ሁለት ዶላር ለማዋጣት</u> የሚችለው ክፍል ብዙ መቶ ሺ እንደሚሆን ይገመታል። ሁልት ዶላር አንድ የስታርባክስ ቡና አይገዛም።***

***አንዳንዶቻችን ሌቦችና ጅቦች እስካሉ ድረስ ለምን ገንዘባችን እንልካለን? እንል ይሆናል። አግባብ አለው። ለዚህ መልሱ አዲሱ ጠ/ሚንስትር የወሰዱት አቋምና የሚመሰርቱት የቁጥጥር ተቋም ነው። ይህ ካልሆነ ድጋፉ ይቆማል።***

***ከአማራጮቹ መካከል ትኩረት የማደርግበት የተጀመሩት ፕሮጀክቶች ባከነው እንዳይቀሩና ድህነትን ለመቅረፍና የምርት ኃይሎችን ለማጎልመስ እንዲቻል የሚከተለውን ጥሪ ለወገኖቸ አቀርባለሁ።***

***አንድ፤ ቤተሰቦቻችን ለመርዳትና ለሌች የግል ጉዳዮችን ለመሸፈን ከምንልከው የውጭ ምንዛሬ ውጭ፤ ከአዲሱ የኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ ዓመት ጀምሮ ለሚከተሉት ዓምስት ዓመታት፤ በየስድስት ወሩ የሚከፈልና የተጀመሩትን የሃዲድ፤ የመስኖ፤ የኃይል ማመንጫና የመንገድ ስራዎች እንዲከናወኑ የሚያስችል የውጭ ምንዛሬ በመሰብሰብ፤ ለእነዚህ ስራዎች በኢትዮጵያ ስም የተገኙ የውጭ ብድሮችን መሸፈን፤ እያንዳንዱ የዲያስፖራ አባል በፈቃደኛነት ተመዝግቦ/ተመዝግባ በቀን $2 ወይም በዓመት $730 ለመስጠት ቃል እንዲገባ/እንድትገባ መተባበር። አበው የሚሉትን "50 ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክም ነው፤ ለአምሳ ሰው ጌጥ ነው" የሚለውን የራሳችን ብሂል መተግበር።***

***ሁለት፤ ከወለሉ በላይ ለመለገስ የሚፈልጉና አቅም ያላቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦች ካሉ ይህን እድል እንዲጠቀሙ ያልተቆጠበ ጥሪት ማድረግ፤ በሰሜን አሜሪካ፤ በአውሮፓ፤ በአውስትራልያና ኒውዚላንድ፤ በደቡብ አፍሪካ ይኖራሉ ተብሎ***

**ከሚገመተው አንድ ሚሊየን ዲያስፖራ 100,000,000 ለመሳተፍ ይችላል የሚለውን ግምት መሰረት በማድረግ በቀን $2,000,000 ሚሊየን፤ በዓመት $720,000,000 ሚሊየን** ሊዋጣ ይችላል።

በአምስት ዓመታት የዲያስፖራው አስተዋጾ ብዙ የውጭ እዳ ይሸፍናል። **የሚላከውን የሚቀራመተው አይኖርም።**

**ሶስት፤ ከመስከረም ጀምረን ለቁጠባ (Savings) የምናስቀምጠውን ዶላርና ሌላ የውጭ ምንዛሬ በከፊል በኢትዮጵያ ሂሳብ ከፍተን እንደ አቅማችን ከ$10,000 እስከ $20,000 ብናስገባና ወለዱን በብር ብንቀበል፤ ካፒታላችን ግን በፈለግነው ጊዜ ያለምንም ገደብ ለማውጣት ብንችል ይህ አስተማማኝ የውጭ ምንዛሬ ያስገኛል። ልጆቻችን ሁሉ እንዲሳተፉ ብናደርግ ጥቅሙ ከፍ ይላል። 100,000 ብቻ ቢሳተፍ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ለማሰብ አይከብድም።**

**ይህ ፕሮጀክት አስተማማኝ የመንግሥት ውሳኔን ይጠይቃል፤ አወንታዊ መልስ እንደሚገኝ  አምናለሁ።**

**አራት፤ እስከ አራት ሚሊየን የሚገመት ዲያፖራ እያለ ለምን መቶ ሺህ በአገር ቤት የባንክ ሂሳብ ይከፈት የሚል ቁጥር ተጠቀምክ፤ አምስት መቶ ወይም አንድ ሚሊየን ቢሆንስ ትሉ ይሆናል። መልካም፤ ሃሳቡ ወለል እንጅ ጣራ አይደለም። ለመሳተፍ ወሰን የለውም፤ ግን በዝቅተኛ መቶ ሽህ ያስፈልጋል።ይህ ፕሮጀክት በመላው ዓለም ለሚኖሩና ለመሳተፍ ለሚችሉ ሁሉ ክፍት ነው። ዋናው ተሳትፎ ነው።**

**አምስት፤ መዋቅር ያስፈልጋል። ይህን የተቀደሰ ስራ ስኬታማ ለማድረግ በዲያስፖራው የሚከበሩና ለአገራቸውና ለመላው ህዝቧ ደህንነት ታማኝነታቸው ከፍተኛ የሆኑ የታወቁ ግለሰቦች፤ ሴቶችን ጨምሮ፤ ገንዝቡ ከተሰበሰበ በኋላ መንግሥት ለሚሰይመው የባንክ ሂሳብ ወደ ኢትዮጵዮጵያ የሚልኩ ከአምስት እስከ ዘጠኝ የሚሆኑ የባለአደራዎች አማካሪ ቡድን ወይም ኮሚቴ እንዲሰየም ማድረግ።**

**እኛ የምናደርገው አስተዋፆ አይሁዶች፤ አርመኖች፤ ፖሊሾች፤ ቻይኒሶችና ሌሎች ካደረጉት ብዙም አይለይም።**

**በራሷ ልጆች የምትመካና የምትኮራ ኢትዮጵያን እንፍጠር!!**

**July 10, 2018**